# ንቃት መፍጠር እና ለውጥ ማምጣት

ተሳታፊዎች ማኅበረሰባቸው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር አንድ ጉዳይ በመለየት እና ያንን ችግር በተመለከተ ሁለት በዚያ ችግር ላይ ሊያዩት ለሚፈልጓቸው ለውጦች ሃሳብ በማመንጨት ስለ ንቃት መፍጠር ጽንሰ ሐሳብ ይማራሉ።

# ንቃት መፍጠር ምንድነው?

## ክፍል አንድ

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

በማኅበረሰባችን እና በአካባቢያችን ዙሪያ የምናደንቃቸው ብዙ ገጽታዎች አሉ። ምናልባት ጓደኞቻችንን እናመሰግን ይሆናል። ምናልባት በአንድ የስፖርት ቡድን ውስጥ መጫወት በመቻላችን ደስ ይለን ይሆናል። ምናልባት ከምንወዳቸው አርቲስቶች አዳዲስ ሙዚቃዎችን የማድመጥ ዕድል ስናገኝ ደስ ይለን ይሆናል።

ነገር ግን፣ በማኅበረሰባችን ውስጥ የማይመቹን ገጽታዎች ይኖራሉ። ምናልባት ትምህት ቤትዎ አቅማችን የማይፈቅደውን ውድ ጨርቅ እንድንጠቀም የሚያስገድድ አዲስ የአለባበስ ደንብ አውጥቶ ይሆናል። ምናልባት የተመረጠ ፖለቲከኛ የእኛን ፍላጎት ያላገናዘቡ ሕጎችን ለማውጣት እየሞከረ ይሆናል። በምንኖርበት አካባቢ ያሉ የመጓጓዣ አማራጮች መሄድ ወደምንፈልግባቸው ቦታዎች እንዲወስዱ ተደርገው አልተሰሩ ይሆናል።

ለምሳሌ ሁላችሁም በአቅራቢያ ወዳለ ሱፐርማርኬት ለመሄድ ሶስት አውቶቡሶችን መሳፈር እና ከዚያም ረጅም መንገድ በእግር መሄድ እንደሚያስፈልግ አስተውላችኋል እንበል።

***ተማሪዎችዎን ይጠይቁ***

*ያንን እንዴት ለመቀየር ሊሞክሩ ይችላሉ?*

ቢጠይቋቸው ሊረዱዎ የሚችሉ ግለሰቦች አሉ?

*ምናልባት እርስዎን የሚያጋጥሙዎት ችግሮች የሚያጋጥማቸው ጓደኞች ሊኖሩዎት ይችላሉ። ሁላችሁም እንዴት ለራሳችሁ መቆም ትችላላችሁ?*

## ክፍል ሁለት

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

በእንዲህ አይነት ሁኔታዎች ውስጥ፣ የሚያሳስቡንን ነገሮች ብንቀይር ነገሮች የተሻሉ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይሰማናል። እንዲህ አይነቱ ለሚያምኑበት ነገር መቆምና ለውጥ መፍጠር ንቃት መፍጠር ይባላል።

**የክላስ መስተጋብር**

በክፍሉ ፊት ለፊት ላይ ባለው የማሳያ ገጽ፣ ንቃት ለመፍጠር የተዘጋጀ የድር ጣቢያ ይመልከቱ። በዚያ ውስጥ የተገለጸው የንቃት መፍጠር አይነት እንዴት በሰዎች፣ ብዙውን ጊዜ ማኅበረሰባቸውን እየጎዳ ያለ

ችግር እንዳለ በተገነዘቡና ያንን ለመለወጥ አንድ ነገር ለማድረግ የፈለጉ ወጣቶች እንተጀመረ አጽንዖት ይስጡ። ከዩናይትድ ስቴትስ ዐውድ የሚጠቀሱ ምሳሌዎች ለ$15 ታገል እና የሴቶች ሰልፍን ያካትታሉ። አለማቀፋዊ አድማስ ያላቸው ምሳሌዎች አለማቀፋዊ ድምጾች፣ አረንጓዴ ሰላም፣ እና የዓለም የዱር እንስሳትን ያካትታሉ።

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

*አሁን በማኅበረሰብዎ ውስጥ እርስዎን በብርቱ የሚያሳስብዎን አንድ ጉዳይና እርስዎን እና ማኅበረሰቡ ችግሩን ለመቅረፍ ሊያደርጉ የሚችሉትን ቀጣይ እርምጃ እንለያለን።*

# ምድብ ሥራ

## ምድብ ሥራ

### ምድብ ስራ

ተሳታፊዎችን በሶስት በ 3 ቡድን ይከፋፍሉ በአሁኑ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ለእያንዳንዱ ቡድን 1) በማኅበረሰባቸው ላይ ተጽዕኖ ያደረሰ ጉዳይ ላይ ጥናት እንዲያደርጉ እና ጉዳዩ ማኅበረሰባቸው ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ ያለባቸውን ቢያንስ ሁለት መንገዶች እንዲሁም ችግሩ ሊፈታባቸው የሚችልባቸውን ቢያንስ ሁለት መፍትሔዎች እንዲያዘጋጁ 2) ስለተለየው ጉዳይና ስለታሰቡት መፍትሔዎች የሚገልጽ ፖስተር እንደ ጋለሪ ጉብኝት ለትትልቁ ቡድን የሚያቀርቡበት ጊዜ ቢያንስ ሁለት ሙሉ ቀናት ይስጡ።

### ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው

በቡድኖችዎ ውስጥ፣

1. ጥናት ያድርጉ እና ስለ ማኅበረሰብዎ (ማኅበረሰብ ማለት ትምህርት ቤትዎ፣ ጉርብትናዎ፣ ወይም እርስዎ ያሉበት ቡድን ሊሆን ይችላል) ሊለውጡት የሚፈልጉትን ገጽታ ይለዩ። ከጓደኞችዎ፣ አስተማሪዎችዎ፣ እና/ወይም ቤተሰብዎ ጋር ሊለውጡት ስለሚፈልጉት ወይም ችግር እያስከተሉባቸው ስላሉ ችግሮች መወያየት ይችላሉ።
2. ፖስተር ይፍጠሩ በእያንዳንዱ ቡድን የሚፈጠሩት ፖስተሮች በግድግዳ ላይ ይሰቀላሉ እናም እኛም በአንድ ላይ የጋለሪ ጉብኝት እናደርጋለን፣ በዚያም እያንዳንዱ ቡድን የለየውን ችግር እና እንዴት እንደሚፈታው ይናገራል።

እያንዳንዱ ቡድን ችግሮቹ ማኅበረሰባቸው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩበትን ቢያንስ ሁለት መንገዶችን እና ቢያንስ ሁለት መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን መለየት አለበት።

ፈጠራዎን ይጠቀሙ፡- ፎቶዎችን ያንሱ እና ችግሩን እና/ወይም መፍትሔዎቹን ለማሳየት በፖስተሩ ላይ ይለጥፉት [ቢቻል፣ ተሳታፊዎች ማተሚያ እንዲያገኙ ይደረግ] ወይም የችግሮቹን እና/ወይም መፍትሔዎቹን ደረጃ ለማሳየት የፍሰት ስዕላዊ መግለጫዎችን፣ ግራፎችን፣ እና ገበታዎችን ይጠቀሙ።

እያንዳንዱ ፖስተር “እራሱን ችሎ መቆም” አለበት - በሌላ አነጋገር፣ ፖስተሩ አንድ ሰው እንዲመለከተው/እንዲያነበው እና የቡድኑ አባል ማብራሪያ ሳያስፈልገው ችግሩ እና መፍትሔው ምን እንደሆነ መረዳት ይችል ዘንድ በላዩ ላይ በቂ መረጃ ሊኖረው ይገባል።

### ምድብ ስራ

ለእያንዳንዱ ቡድን ጥናቱን እንዲያጠናቅቅ እና ፖስተሩን እንዲያዘጋጅ በቂ ጊዜ ይስጡት። ለጥያቄ እና ለቴክኒካዊ ድጋፍ እራስዎን ዝግጁ ያድርጉ። ትልቁ ቡድን በሚሰበሰብ ጊዜ፣ ተሳታፊዎች ፖስተሮቹን በግድግዳ ላይ እንዲሰቅሉ ያድርጉ፣ ለትልቁ ቡድን እየተዘዋወሩ የለሎቹን ፖስተሮች እንዲመለከቱ 20 ደቂቃዎች ይስጡ፣ ከዚያም እያንዳንዱ ትንንሹ ቡድን የየራሳቸውን ፖስተር ለትልቁ ቡድን እንዲያቀርቡ 30 ደቂቃ ይስጡ።

ይህ መማሪያ ነገር በ Berkman Klein Center for Internet &amp ላይ በወጣት እና ሚድያ የቀረበ ነው; ሃርቫርድ ዩኒቨርስቲ ሶሳይቲ በ Creative Commons Attribution-ShareAlike 4.0 International ፈቃድ ስር። ወጣት እና ሚድያን እንደ ኦርጂናል ምንጭ እስከጠቀሱ እና ተጨማሪ ስራዎችን በተመሳሳይ ስምምነት መሰረት እስካከናወኑ ድረስ ከሱ የተወሰዱ ንግዳዊም ንግዳዊ ያልሆኑም ከሱ የተወሰዱ ነገሮች መጠቀም ይችላሉ። እነዚህን እና ተጨማሪ መማሪያ ነገሮችም Berkman Klein's Digital Literacy Resource Platform መስመር ላይ ይገኛሉ።